# ማሽከርከር እና የተሽከርካሪ ደህንነት

## Requirement Specification

**አጠቃላይ ሐሳብ**

ይህ መመሪያ ከማሽከርከር እና የተሽከርካሪ ደህንነት ጋር በተያያዘ የኤሪክሰን ግሎባል የጤና፣ ደህንነት እና ጤናማ ሁኔታ (HSW) መስፈርቶችን ይገልጻል።

**ተፈጻነሚት**

ይህ መመሪያ ለኤሪክሰን አቅራቢዎች፣ ለአቅራቢዎች ሰራተኞች እንዲሁም በኩባንያው ውስጥ በባለቤትነት፣ በኪራይ፣ ወይም በግል ባለቤትነት የተመዘገቡ ሁሉም ተሽከርካሪዎችን ለሚያሽከረክሩ ሰራተኞችን ይመለከታል። (ከሥራ ወደ ሥራ መሄድ አይካተትም)።

ይህ መመሪያ በኩባንያ ስራ ላይ የተሽከርካሪ አጠቃቀምን ይመለከታል፣ ይህ ማለትም ለስራ ጉዳይ ወደ ስራ ቦታዎች ለመሄድና ለመመለስ መንዳት ይመለከታል፣ የግል ወይም የኪራይ መኪና ለስራ ጉዳይ መንዳትንም ይጨምራል።

ከኤሪክሰን የአካባቢ ድርጅቶች፣ ደንበኞች፣ የድርጅት ባለቤቶች ወይም የአካባቢ ደንቦች የበለጠ ጥብቅ ወይም የበለጠ ገደብ ያላቸው መስፈርቶች ከሆኑ እነዚህ መስፈርቶች ሁልጊዜ በዚህ መስፈርት ውስጥ ያለውን ተዛማጅ ዝርዝር ይተካሉ።

 © Ericsson AB 2025 

**ማውጫ**


**1 መመሪያ ... 4**
1.1 አጠቃላይ ... 4
**2 የቅድመ-ማሽከርከር መስፈርቶች። ... 5**
2.1 የስጋት ጥናት። ... 5
2.2 የቅድመ-ማሽከርከር ፍተሻ – የፕሮጀክት ተሽከርካሪዎች ብቻ። ... 6
2.3 የጉዞ ቁጥጥር እቅድ – ለፕሮጀክት ተሽከርካሪዎች ብቻ። ... 7
**3 የአሽከርካሪ መስፈርቶች። ... 8**
3.1 የማሽከርከር ገደቦች። ... 8
3.2 ለማሽከርከር ብቁ መሆን። ... 9
3.3 የአሽከርካሪዎች ኦሬንቴሽን/ስልጠና። ... 10
3.3.1 የአሽከርካሪ ኦሬንቴሽን። ... 10
3.3.2 ኤሪክሰን ደህንነቱ የተጠበቀ የማሽከርከር ግንዛቤ። ... 10
3.3.3 ተከላካይ/አስተማማኝ ማሽከርከር። ... 10
3.3.4 ከዋና መንገድ ውጭ ያሉ መንገዶች ወይም አራቱንም ጎማዎች ማንቀሳቀስ በሚችል መኪና ማሽከርከር። ... 11
3.4 የማሽከርከር አፈጻጸም ክትትል ... 11
3.4.1 የክትትል ሂደት። ... 11
**4 የተሽከርካሪ መስፈርቶች። ... 12**
4.1 የተሽከርካሪ የደህንነት መሳርያዎች። ... 12
4.2 ከዋና መንገድ ውጭ ላሉ መንገዶች የተሰሩ ተሽከርካሪዎች ያሏቸው የደህንነት መሳርያዎች፡- ... 13
4.3 መጎተት፣ ተሳቢዎች እና ከመጠን በላይ የሆኑ ጭነቶች። ... 13
**5 ሌሎች የተሽከርካሪ ዓይነቶች እና ለስራ አጠቃቀሞች። ... 14**
5.1 ሞተርሳይክሎች (ባለ ሁለት ጎማ ተሽከርካሪዎች)። ... 14
**6 ኃላፊነቶች ... 15**
6.1 አሽከርካሪዎች። ... 15
6.2 የሥራ ኃላፊ (PICW) / የቡድን መሪ ወይም ተመሳሳይ ኋላፊነት ያለው። ... 15
6.3 የአቅራቢ ፕሮጀክት ኋላፊዎች። ... 16
6.4 የተሽከርካሪዎች አስተዳዳሪ፣ የተሽከርካሪዎች አስተባባሪ፣ ወይም ተመሳሳይ ኋላፊነት ያለው ... 16
**7 ማጣቀሻዎች። ... 17**
**8 የተቀየረ መረጃ። ... 17**


 © Ericsson AB 2025 

# 1 መመሪያ

## 1.1 አጠቃላይ

- በማከናወን ብቃትዎ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ የታዘዙ መድኃኒቶችን ጨምሮ በአልኮል ወይም በአደገኛ ዕጾች ተጽዕኖ ሥር ፈጽሞ መሥራት ወይም ማሽከርከር የለብዎትም። ሕይወት አድን ሕጎች

- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ወይም የተሽከርካሪ ተሳፋሪ በሚሆኑበት ጊዜ ሁልጊዜ የደህንነት ቀበቶ ያድርጉ። ሕይወት አድን ሕጎች

- የፍጥነት ገደቦች መታለፍ የለባቸውም። ሕይወት አድን ሕጎች

- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ በእጅ የሚያዙ ስልኮችን ወይም መሳሪያዎችን በጭራሽ አይጠቀሙ። ሕይወት አድን ሕጎች ይህም የሞባይል መልእክት፣ የቪዲዮ ጥሪዎች፣ የድምጽ ጥሪዎችን ያካትታል። በድምጽ ማጉያ በኩል ለመነጋገር ብሉቱዝ ወይም ተመሳሳይ አይነት የግንኙነት መስመር መጠመቀም ይቻላል። አሽከርካሪዎች በሚያሽከረክሩበት ጊዘ የጆሮ ማዳመጫዎችን ወይም ሄድፎኖች መጠቀም የለባቸውም።

- በፕሮጀክቱ፣ በአገር ወይም በክልል እንዲሁም በክፍል ደረጃ የሚካሄደው የስጋጥ ጥናት (ክፍል 2.1 ይመልከቱ) የማሽከርከር እና የተሽከርካሪ ደህንነትን ይጨምራል።

- ተሽከርካሪው በሚሄድበት መንገድ በሙሉ የሞባይል ስልክ ኔትወርክ ሽፋን የሌላቸው የታወቁ ቦታዎች ካሉ አሽከርካሪው ለብቻው መንዳት የለበትም።

- ሁሉም አሽከርካሪዎች ህጋዊ እና ወቅታዊ የመንጃ ፍቃድ መያዝ እና የተመደበውን የተሽከርካሪ አይነት/ክፍል ለማሽከርከር የአካባቢ ህጋዊ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው።
- 
- የሚፈቀድ ከሆነ፣ በተሽከርካሪ ውስጥ የሚገጠም የክትትል ስርዓት (IVMS)/ቴሌማቲክስ መጠቀም በጥብቅ ይመከራል። IVMS/ቴሌማቲክስ መሳሪያዎች በተጫኑባቸው መኪናዎች፣ የአሽከርካሪዎች ባህሪ በየጊዜው ክትትል ሊደረግበት ይገባል።

- አሽከርካሪዎች የሚነዱትን ተሽከርካሪዎች አሠራር እና መቆጣጠርያ ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው።

- አሽከርካሪዎች እና ተሳፋሪዎች በማናቸውም ጊዜ ተሽከርካሪው ውስጥ ማጨስ ወይም ቬፒንግ መጠቀም የተከለከለ ነው።

- ፍቃድ ያልተሰጣቸው ተሳፋሪዎች (ማለትም ከአሽከርካሪው ጋር በተገናኘ ከተመደበው የስራ ወሰን ጋር ያልተያያዙ ሰራተኞች) እና የመንገድ ተሳፋሪዎች የተከለከሉ ናቸው።

- ተሳፋሪዎች በጭነት ቦታ ወይም በተሽከርካሪ ወለል፣ በፒክ አፕ መኪና ወዘተ መሳፈር የለባቸውም።

- በተሽከርካሪው ውስጥ ያሉ መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶች እንቅስቃሴን ለመገደብ በጥንቃቄ መታሰር አለባቸው።

- ተሽከርካሪዎች ከምዝገባ፣ ኢንሹራንስ ጋር የተያያዙ ሁሉንም የአካባቢ ደንቦች ያሟሉ እንዲሁም ለተፈለገው ዓላማ ተስማሚ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ያሉ መሆን አለባቸው።

- ተሽከርካሪዎች በአካባቢው ህጋዊ ደንቦች መሰረት የፍተሻ ፕሮቶኮሎችን ማክበር አለባቸው።

- ተሽከርካሪዎች በተሽከርካሪ ሻጭ ወይም አምራች ለተገለጸው የጥገና መርሃ ግብር ተገዢ መሆን አለባቸው። ደህንነታቸው ባልተጠበቀ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ተሽከርካሪዎች ሊነዱ አይገባም፣ ጥገና እስኪደረግላቸው ድረስም ከአገልግሎት ውጪ መሆን አለባቸው። የጥገና መዝገቦች በጥያቄ መሰረት ለኤሪክሰን ሊቀርቡ የሚችሉ መሆን አለባቸው።

- ተሽከርካሪዎች በአምራቹ ከተጠቀሰው ከፍተኛ የመጫን አቅም በላይ መጫን የለባቸውም።

- ማንኛውንም አደገኛ ሁኔታዎች ከተመለከቱ፣ ከአደጋ ለትንሽ የማምለጥ ክስተት ከነበረ፣ እንዲሁም አደጋ ከተከሰተ የአደጋው ምንጭ ለማጣራት እና አስፈላጊ እርምጃ ለመውሰድ እንዲረዳ ያጋጠመውን ሁኔታ በአለምአቀፍ የክስተት ሪፖርት ማቅረቢያ መሳሪያ (GIRT) ውስጥ ሪፖርት ያድርጉ።

- በየሥራ ማቆም ባለስልጣን መመሪያ [1] መሰረት በዚህ ጽሑፍ የዘረዘሩትን መመሪያዎች የማያሟላ አሽከርካሪ ወይ ተሽከርካሪ የተመለከቱ አሽከርካሪዎች እና ተሳፋሪዎች በGIRT ውስጥ ስጋታቸውን ሪፖርት እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

- በክፍል 2.2 መሠረት የተሽከርካሪውን ደህንነቱ የተጠበቀ ማሽከርከር ለማረጋገጥ የቅድመ-ማሽከርከር ፍተሻ ወይም ምርመራ ይከናወናል።

- በክፍል 2.3 መሠረት የጉዞ ቁጥጥር እቅድ ይከናወናል።

# 2 የቅድመ-ማሽከርከር መስፈርቶች።

## 2.1 የስጋት ጥናት።

በአንድ ፕሮጀክት የሚደረግ የስጋት ጥናት የማሽከርከር እና የተሽከርካሪ ደህንነት አደጋን ማካተት አለበት። ቢያንስ የሚከተሉት ነገሮች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡-

- የማሽከርከር አስፈላጊነት (ማለትም ስራው በአካል መገኘት ሳያስፈልግ ሊጠናቀቅ ይችላል? ወይም ሌሎች አስተማማኝ የመጓጓዣ ዘዴዎች አሉ?)።
- የአየር ሁኔታ (የአሁኑ እና ትንበያ)።
- በጨለማ ሰዓታት ማሽከርከር።
- በአማካይ በየቀኑ የሚጓዙት ርቀቶች።
- ሊያጋጥሙ የሚምችሉ የመሬት አቀማመጥ፣ የመንገድ ሁኔታ እና የትራፊክ ሁኔታዎች።
- የተሽከርካሪው ሁኔታ እና ሁሉም የደህንነት መሳሪያዎች።
- ሊያጋጥሙ የሚችሉ የደህንነት ሁኔታዎች።
- የተንቀሳቃሽ ስልክ አውታረ መረብ ሽፋን መኖሩን እና አለመኖሩ።
- ሊከሰቱ የሚችሉ ድንገተኛ አደጋዎች እና የአደጋ ጊዜ አገልግሎቶች መገኘት።
- የአሽከርካሪዎች ልምድ እና ብቃት።
- አዳር አስፈላጊ ከሆነ ማደርያ ቦታ መኖሩ።

 © Ericsson AB 2025 

- ለኩባንያው ስራ አልፎ አልፎ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የታቀዱ የግል ባለቤትነት ያላቸው ተሽከርካሪዎች።
- እየተገመገመ ባለው ፕሮጀክት/አካባቢ የሚታወቁ ወይም ያሉ ከላይ ያልተዘረዘሩ ሌሎች አደጋዎች።

አግባብነት ያለው የቁጥጥር እርምጃዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተገለጹት መስፈርቶች መሰረት መገለጽ አለባቸው፣ እንዲሁም አሽከርካሪውን፣ ተሳፋሪዎችን፣ ህዝብን ወይም ሌላ የሚመለከተውን አካል መጠበቅ እንዲቻል ተለይተው የሚታወቁትን አደጋዎች ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ መተግበር አለባቸው።

የቁጥጥር እና ቅነሳ እርምጃዎች ከተወሰዱ በኋላ ያለው ቀሪ የአደጋ ደረጃ አሁንም ከፍተኛ ወይም በጣም ከፍተኛ ነው ተብሎ ከታሰበ ወደ ከሰራተኞች ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አስተዳዳሪ ወይም ኃላፊነት ያለው EHS SME ይደርሳል። የአደጋው ደረጃ ከፍተኛ ከሆነ ወይም በጣም ከፍተኛ ከሆነ ማሽከርከር አይፈቀድም።

## 2.2 የቅድመ-ማሽከርከር ፍተሻ – የፕሮጀክት ተሽከርካሪዎች ብቻ።

- የቅድመ ማሽከርከር ፍተሻ በአሽከርካሪው በየቀኑ የመጀመሪያው ጉዞ ከማድረጉ በፊት ይካሄዳል። እንዲፈተሹ የሚመከሩ ነገሮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

ተሽከርካሪ፦

- የአሽከርካሪ እና የሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶዎች።
- የፊት መብራቶች፣ የፍሬን መብራቶች፣ የመታጠፍያ ምልክቶች መብራቶች፣ የአደጋ መብራቶች (ሁሉም መብራቶች የሚሰሩ ከሆነ)።
- የመኪና ጥሩንባ።
- የመኪና መስኮቶችና መስታወቶች (ንጹህ እና ያልተሰነጠቀ)።
- የዝናብ መጥረጊያዎች እና በቂ የመጥረግያ ፈሳሽ ካላቸው።
- ጎማዎች ጤናማ መሆናቸው።
- መለዋወጫ ጎማ እና የጎማ መለዋወጫ መሳሪያዎች (በአገልግሎት ውል ውስጥ ካልተካተቱ)።
- የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ቁሳቁስ፣ የድንገተኛ አደጋ ቁሳቁስ (የማስጠንቀቂያ ኮኖች/ትሪያንግል ጨምሮ)፣ የእሳት ማጥፊያ።
- ከመኪናው የሚፈስ ነገር ካለ።

ሾፌር፦

- የአሽከርካውች ድካም እና የጤና ሁኔታ።
- የኋላ እይታ መስተዋቶች ማስተካከል (የማይታዩ ቦታዎችን ለመቀነስ)።
- መቀመጫ እና የመኪና መሪ ማስተካከል (አስፈላጊ ከሆነ)።

- ሰነድ፦
- የመንጃ ፍቃድ የሚያበቃበት ቀን።
- በህጋዊነት የሚያስፈልጉ የተሽከርካሪ ሰነዶች (ማለትም፣ መለያዎች፣ ምዝገባ፣ ኢንሹራንስ፣ የአምራች መመሪያ)።

- በቅድመ ማሽከርከር ፍተሻ ወቅት የተገኘ ጉድለት መታረም አለበት። ጉድለቶቹ ለአሽከርካሪ እና ለተሳፋሪዎች አደጋን ማስከተላቸው የማይቀር ከሆነ ማሽከርከር አይፈቀድም።

## 2.3 የጉዞ ቁጥጥር እቅድ – ለፕሮጀክት ተሽከርካሪዎች ብቻ።

ሊደረግ የታቀደው ጉዞ በስጋት ጥናቱ (ክፍል 2.1) ያልተሸፈነ አደጋ፣ እንዲሁም ያልተለመደ ወይም ለተሽከርካሪ/ለሾፌሩ በተለየ ሁኔታ ወይም ለታቀደው የመጓጓዣ አገልግሎት፣ ለሚጓዙበት መንገዶች፣ ለስራ አከባቢው፣ ወይም ከመነሻው ቦታ ከመሄድና ከመመለስ ጋር በተያየዘ ማንኛውም ሁኔታ አደጋ እንዳለው አስቀድሞ ሲታወቅ፣ ጉዞው ከመጀመሩ በፊት መላው ጉዞውንና የመመለሻ ጉዞዎች የሚሸፍን፣ አደጋዎችን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዳ እርምጃዎችን በመለየት የጉዞ ቁጥጥር እቅድ (JMP) መከናወን አለበት።

ከአንድ ጉዞ ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ያልተለመዱ አደጋዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦-

- ከዚህ ቀደም ያልተመዘገበ/ያልተረጋገጠ አዲስ ወይም የተለየ አሽከርካሪ/ተሽከርካሪ።
- እጅግ በጣም ርቀው የሚገኙ ቦታዎች እና የስራ አከባቢዎች (ማለትም፣ ህዝብ ከሚኖርበት ወይም የድንገተኛ አደጋ አገልግሎቶች ካሉበት ርቆ የሚገኝ)።
- ረጅም የማሽከርከር ጉዞዎች (ማለትም፣ ከ400 ኪሎ ሜትር (250 ማይል) ወይም አራት ሰአታት በላይ)።
- ከዋና መንገድ ውጭ ያሉ መንገዶች።
- ከመጠን በላይ ጭነቶች የጫነ ተጎታች መጎተት።

የጉዞ ቁጥጥር እቅድ (JMP) እንደሚከተሉት ያሉ የተወሰኑ አደጋዎችን ይገመግማል፦-

- የአሽከርካሪው ጤና እና የአዕምሮ ሁኔታ (ለምሳሌ፣ ያልተገባ ጭንቀት፣ ትኩረት መከፋፈል እና ግፊቶች)።
- የአሽከርካሪዎች አጠቃላይ ልምድ እና አፈፃፀም።
- አጠቃላይ የስራ ሰአታት፣ የመንዳት ጊዜን ጨምሮ።
- በጨለማ ሰዓታት ውስጥ ማሽከርከር።
- የመንገዶች ዓይነቶች (ማለትም፣ ዋና ዋና አውራ ጎዳናዎች፣ ባለ ሁለት መስመር መንገዶች፣ ዋሻዎች፣ ድልድዮች፣ በግንባታ ላይ ያሉ ቦታዎች፣ ኮረኮንቻማ መንገዶች፣ ጉድጓድ የበዛበት መንገድ፣ አደገኛ ኩርባዎች፣ ገደላማ ቁልቁለቶች፣ ወዘተ.)።
- ሊገመቱ የሚችሉ ወይም የሚታወቁ የትራፊክ/የመንገድ ሁኔታዎች (ማለትም፣ በመንገድ የሚያጋጥሙ እግረኞች፣ ለጎርፍ የተጋለጡ አካባቢዎች፣ በብልሽት ጊዜ የሚቆምበት የመንገድ ዳር የሌላቸው መንገዶች፣ በገደል ዳር፣ የመሬት መንሸራተት ሊያጋጥም የሚችሉባቸው ቦታዎች፣ ጉድጓድ የበዛበት መንገድ፣ የከባድ መኪናዎች በመንገድ ላይ መኖር፣ የትራፊክ መጨናነቅ፣ የአንድ አቅጣጫ መንገድ፣ ጎህ ሲቀድ/አመሻሽ ላይ ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን ያለበት፣ በቂ የመንገድ መብራት የሌለበት፣ በቂ የትራፊክ ምልክቶች የሌለበት፣ እንስሳት በመንገድ ላይ ሊገቡ የሚችሉበት፣ ባቡር የሚያቋርጥበት ወዘተ)
- የአሁኑ እና የተተነበዩ የአየር ሁኔታ ሁኔታዎች።
- መድረሻው ላይ ሲደርሱ የሚገናኙት ሰው መረጃ ወይም የመግቢያ መረጃ (ለምሳሌ ስሞች እና ስልክ ቁጥሮች)።
- የሞባይል ስልክ ሽፋን እንደሌላቸው የሚታወቁ ወይም ሊሆኑ የሚችሉ አካባቢዎች።
- የእረፍት እና የምግብ መገልገያዎች ቦታዎች መገኘት።
- የእረፍት እቅድ፣ ቦታ እና ማረፊያ።
- በቂ ፈሳሽ ለማግኘት የሚያስችል አቅርቦት።

- የሚጓጓዙት እቃዎች እና/ወይም ቁሳቁሶች ክብደት፣ ቁመት እና ርዝመት ከተሽከርካሪው ስፋት እና ከመንገዱ መሠረተ ልማት አንጻር (ለምሳሌ ድልድይ፣ ማለፊያዎች፣ ተደራራቢ ድልድዮች ወዘተ)
- በተሽከርካሪው ውስጥ ያሉ መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶች እንቅስቃሴን ለመገደብ እንዴት እንደሚታሰሩ።
- የነዳጅ ማደያ / የመኪና ባትሪ ሞምያ ቦታዎች።
- የአደጋ ጊዜ እቅድ ቢያንስ፣ የድንገተኛ አደጋ ቁጥሮች፣ በአቅራቢያ ያሉ የህክምና ማዕከላት እና የአደጋ ጊዜ አስተዳደር አቅማቸው፣ በተሽከርካሪ ውስጥ ያሉ የድንገተኛ አደጋ መሳሪያዎች ዝርዝሮች እና የሰራተኞች የድንገተኛ አደጋ ስልጠና የሚያጠቃልል መሆን አለበት።
- ወደ መድረሻው እና በመድረሻው አከባቢ የመዳረሻ መንገዶች።

# 3 የአሽከርካሪ መስፈርቶች።

## 3.1 የማሽከርከር ገደቦች።

ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ የሚታየው ከፍተኛው የማሽከርከር ሰዓቶች ብዛት መከተል አለብዎት። እነዚህ በሰንጠረዡ ውስጥ የተገለጹት ከፍተኛው የማሽከርከር ሰዓቶች ስራን ለማከናወን ወይም ለቅልጥፍና ተብሎ ሊደረስበት እንደሚገቡ ግብ ተደርገው የማሽከርከር ጊዜ ለመመደብ ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።

በተቻለ መጠን በጨለማ ሰአታት፣ በተለይም ከፍተኛ የአካል/የግንዛቤ ጥረት ከሚጠይቅ ከረዥም የስራ ፈረቃ በኋላ በጨለማ ሰአታት ከማሽከርከር ይቆጠቡ።

| | ከፍተኛው የማሽከርከር ሰዓቶች ብዛት |
|---|---|
| ከፍተኛው የማሽከርከር ግዜ | • በስራ ፈረቃ ውስጥ አንድ አሽከርካሪ በተሽከርካሪው ላይ የሚቆይበት ከፍተኛው ጊዜ ድምር 10 ሰዓታት ብቻ መሆን አለበት።<br>• አሽከርካሪው ከ10 ሰአታት በላይ እንዲሰራ ከተጠበቀ፣ ጉዞው ለሁለት ቀናት መከፈል አለበት (እንዲሁም ተገቢ ማረፊያዎች መዘጋጀት አለበት)።<br>• በየ2 ሰዓቱ የ15 ደቂቃ ዕረፍት ለማድረግ መታቀድ አለበት።<br>• በሁለት ሰአታት የመንዳት ጊዜ ውስጥ አስተማማኝ ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ የማረፍያ ቦታ ከሌለ፣ ማረፊያ ቦታ ልክ እንደተገኘ ወድያውኑ አቁመው እረፍት ያድርጉ።<br>• አሽከርካሪዎች ከመጀመሪያው የስራ ፈረቃ በፊት በደንብ ማረፍ አለባቸው፣ ለምሳሌ፣ የስምንት ሰአት ያልተቆራረጠ እረፍት ማድረግ አለባቸው። |

| | |
|---|---|
| | • ሹፌሩ ወደ ሩቅ ቦታ ነድቶ ከፍተኛ አደጋ ሊኖረው የሚችል የመስክ ስራን እንዲያከናውን ወይም እንዲቆጣጠር የሚጠበቅበት ከሆነ፣ ወደ ቦታው ለሚሄድና ለመመለስ የሚፈጅበትን አጠቃላይ ጉዞ ከአራት ሰአት መብለጥ የለበትም። <br><br> • ወደ ሥራ ቦታ ማሽከርከር በጨለማ ሰዓታት ውስጥ መከናወን ካለበት እያንዳንዱ ጉዞ ቢበዛ በሁለት ሰዓታት ለመገደብ ጥረት ይደረጋል። <br><br> • ከመመለሻ ጉዞው በፊት አሽከርካሪዎች በመንዳት አፈጻጸምን እና ደህንነትን ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል በሰሩት ስራ ምክንያት በአካላዊ፣ ጤና እና አእምሯዊ ሁኔታቸው ላይ አጋጥሟቸው ሊሆን የሚችል ማንኛውንም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ወደ ከሰራተኞች ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አስተዳዳሪ/ ተቆጣጣሪ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። |

## 3.2 ለማሽከርከር ብቁ መሆን።

- ሁሉም አሽከርካሪዎች ለመንዳት ብቁ መሆን አለባቸው፣ ይህም በአሽከርካሪነት ስራው ጊዜ ሁሉ ጥሩ እረፍት ያገኙና እና ንቁ መሆንን ይጨምራል።

አሽከርካሪዎች በአደገኛ ዕፆች ወይም በአልኮል ተጽእኖ ሥር መሆን የለባቸውም፣ ይህም በአስተማማኝ የማሽከርከር ስራ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ያለ ሐኪም ማዘዣ የሚወሰዱ ወይም የታዘዙ መድኃኒቶች እንዲሁም ደክመው እያሉ ማሽከርከርን ያጠቃልላል።

- አሽከርካሪዎች ማንኛውም ማሽከርከር ስራ ከማከናወናቸው በፊት አካላዊ እና አእምሯዊ ዝግጁነታቸውን ራሳቸው እንዲገመግሙ ይመከራሉ። ይህ ራስን መገምገም የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

- አካላዊ ጤንነት፡- አሽከርካሪው በአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና በህመም ምልክቶች ወይም በማንኛውም መድሃኒት ምክንያት ትኩረትን ሊጎዳ ወይም አፈፃፀሙን ሊጎዳ ከሚችል ከማንኛውም የጤና ሁኔታ ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።
- እረፍት፡- አሽከርካሪው ንቁ እንዲሆን እና ትኩረት እንዲያደርግ ስራዎችን ከመጀመሩ በፊት በቂ እረፍት እና እንቅልፍ ማድረጉን ማረጋገጥ አለበት።
- በቂ ፈሳሽ መጠጣት፡- አሽከርካሪው በቂ ፈሳሽ መጠጣቱን ማረጋገጥ አለበት።
- ኤሮኖሚክስ፡- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ አላስፈላጊ አካላዊ ጫናዎችን ለመከላከል የሰውነት አቀማመጥ እና የመቀመጫ አቀማመጥ ትኩረት ይስጡ።
- የአእምሮ ጤንነት፡- የመረጋጋት ስሜትን እና አእምሮአዊ ትኩረትን ይኑርዎት፣ እንዲሁም በህመም ምልክቶች ወይም በማንኛውም መድሃኒት ምክንያት ትኩረትን ሊጎዳ ወይም የደህንነት ስራን ሊጎዳ ከሚችል ከማንኛውም የጤና ሁኔታ ነጻ መሆኑዎን ያረጋግጡ።

- አሽከርካሪዎች የመንዳት አፈጻጸም ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የአእምሮ ወይም የጤና እክል (ለምሳሌ ያልተገባ ጭንቀት፣ ትኩረት የሚከፋፍሉ እና ግፊቶች) ካጋጠማቸው

ከሰራተኞች ቀጥተኛ ግንኙነት ላለው አስተዳዳሪ ወይም ለተቆጣጣሪ ማሳወቅ እና ችግሮችን ለመከላከል ወይም ለማቃለል በሚያስችል እርምጃዎች ላይ መስማማት አለባቸው።

## 3.3 የአሽከርካሪዎች ኦሬንቴሽን/ስልጠና።

ለኤሪክሰን ወይም ኤሪክሰንን ወክለው ሲሰሩ ተሽከርካሪን የሚጠቀሙ ሁሉም አቅራቢዎች የሚከተለውን ኦሬንቴሽን/ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡-

### 3.3.1 የአሽከርካሪ ኦሬንቴሽን።

ተሽከርካሪን ለመጀመሪያ ጊዜ በኩባንያው ሥራ ላይ ከማሽከርከራቸው በፊት ለአዲስ ተቀጣሪዎች እና/ወይም ሹፌሮች የተዘጋጀውን ኦሬንቴሽን ማጠናቀቅ አለባቸው።

የአሽከርካሪ ኦሬንቴሽን ከሰራተኞች ቀጥተኛ ግንኙነት ባለው አስተዳዳሪ፣ ተቆጣጣሪ፣ የደህንነት ሰራተኞች ወይም የተሽከርካሪዎች አስተዳደር ሰራተኞች መሰጠት አለባቸው። የአሽከርካሪ ኦሬንቴሽን አቀማመጥ እንደሚከተሉት ያሉ ርዕሶችን ለመሸፈን የታሰበ ነው፡-

- ለሚነዳው ተሽከርካሪ ክፍል የሚመለከት ህጋዊ እና ወቅታዊ የመንጃ ፍቃድ ማረጋገጫ።
- ተፈፃሚነት ያለው ኤሪክሰን የህይወት አድን ህጎች።
- የቅድመ-ማሽከርከር ፍተሻ እና የጉዞ ቁጥጥር ዕቅድ መስፈርቶች።
- ለማሽከርከር ብቁ የመሆን መስፈርቶች።
- የዚህ መመሪያ ሌሎች ተዛማጅ መስፈርቶች።
- የተመደበው ተሽከርካሪ የመቆጣጠሪያዎች ስራ።
- ልዩ የአካባቢ ወይም የአቅራቢዎች ተሽከርካሪዎች ቊጥጥር እና የተሽከርካሪ አጠቃቀም ደንቦች እና ዝግጅቶች።
- የትራፊክ ህጎችን የሚጥሱ ወይም በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ መስፈርቶችን የማያሟሉ አሽከርካሪዎች የሚደርሷቸው መዘዞች።
- በኤሪክሰን አለምአቀፍ የክስተት ሪፖርት ማቅረቢያ መሳሪያ (GIRT) ውስጥ ክስተቶችን መቼ እና እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል።

### 3.3.2 ኤሪክሰን ደህንነቱ የተጠበቀ የማሽከርከር ግንዛቤ።

በጣም ወቅታዊ የሆኑትን በኦንላይን የሚገኙ የኤሪክሰን ደህንነቱ የተጠበቀ የማሽከርከር ስልጠናን በየዓመቱ ያጠናቅቁ፡-

በደህና ቤትዎ ይድረሱ

### 3.3.3 ተከላካይ/አስተማማኝ ማሽከርከር።

ቢያንስ በየሁለት ዓመቱ በአካል በመገኘት፣ በአካባቢው የሚሰጥ የተከላካይ/አስተማማኝ የማሽከርከር ስልጠና ያጠናቅቁ።

ትምህርቱ ቢያንስ አራት ሰአታት የሚሸፍን ሲሆን፣ የክፍል እና በመኪና መሪ በመሆን (ተግባራዊ) የሚሰጡ ስልጠናዎች እንዲያካትት ይመከራል።

የተከላካይ የማሽከርከር ስልጠናዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና ባለው የስልጠና አቅራቢ እንዲሰጡ ይመከራል። እንደዚህ አይነት አሰልጣኝ የማይገኝ ከሆነ፣ ትምህርቱን እንደዚህ አይነት ስልጠና ለመስጠት ብቃት ባላቸው እና የተከላካይ የማሽከርከር ዘዴ እውቀት ባያላቸው የኤሪክሰን ሰራተኞች መሰጠት ይችላል። ኮርሱ የእውቀት ፈተናን ያካትታል፣ እንዲሁም የተሳትፎ የምስክር ወረቀት ይኖረዋል።

ማሳሰቢያ፡- የተከላካይ የማሽከርከር ስልጠና አደጋዎችን ለማስወገድ እና/ወይም የትራፊክ አደጋዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ተከታታይ ቴክኒኮችን እና ልምምዶችን ያቀፈ ነው። በመከላከያ የማሽከርከር ኮርስ ውስጥ የሚካተቱት አጠቃላይ ጭብጦች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የአሽከርካሪውን በትኩረት የመከታተል መስክ ማስፋት።
- ቀጣይነት ያለው የእይታ ፍለጋ።
- ስለ አካባቢው አጠቃላይ የግንዛቤ ንቃት መኖር።
- የሌሎች ድርጊቶች ቀድሞ መገመት።
- ቀድሞ ማቀድ።
- ወቅታዊ እና ሆን ተብሎ የሚደረጉ ድርጊቶች/ምላሾች።
- ድካም ማስወገድ።

### 3.3.4 ከዋና መንገድ ውጭ ያሉ መንገዶች ወይም አራቱንም ጎማዎች ማንቀሳቀስ በሚችል መኪና ማሽከርከር።

ከዋና መንገድ ውጭ በሆኑ መንገዶች ላይ እንዲያሽከረክሩ የተመደቡ አሽከርካሪዎች ቢያንስ በየሁለት አመቱ አራቱንም ጎማዎች ማንቀሳቀስ የሚችል መኪናን በአስተማማኝ ሁኔታ የማሽከርከር ክህሎቶችን በተግባር ስልጠና ማጠናቀቅ አለባቸው።

- አራቱንም ጎማዎች ማንቀሳቀስ የሚችል መኪና ትራንስሚሽን።
- በተለያዩ ከዋና መንገድ ውጭ የሆኑ መንገዶች የማሽከርከር ዘዴዎች።
- መኪናን መልሶ የመቆጣጠር ዘዴዎች።
- ከዋና መንገድ ውጭ በሆኑ መንገዶች ሲያሽከረክሩ ሊኖርዎት የሚገባ የተለያዩ መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶች  አጠቃላይ ይዘታ

## 3.4 የማሽከርከር አፈጻጸም ክትትል

ጥሩ አፈጻጸምን ለመለየት እና የሚሻሻሉ/ያልተተገበሩ ነገሮች ለማወቅን ለመቅረፍ የማሽከርከር አፈጻጸም ክትትል ሊደረግበት ይገባል።

### 3.4.1 የክትትል ሂደት።

የማሽከርከር አፈፃፀም በሚመለከተው ደንብ እና ህግ መሰረት፣ በአሽከርካሪዎች በየጊዜው (ለምሳሌ፣ ወርሃዊ) ተሰብስቦ መተንተን አለበት፣ እንዲሁም ከሰራተኞች ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አስተዳዳሪ/ ተቆጣጣሪ የመሳሰሉት ኋላፊዎች ደግሞ ጥሩ አፈጻጸም በማድነቅ እና የታዩ ችግሮችን ትኩረት በመስጠት ለአሽከርካሪዎቹ አስተያየት መስጠት አለባቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተገኘው ውጤት ላይ ትኩረት ያደረገ አስተዳደራዊ እርምጃዎች መወሰድ አለበት።


© Ericsson AB 2025

# 4 የተሽከርካሪ መስፈርቶች።

## 4.1 የተሽከርካሪ የደህንነት መሳርያዎች።

በኩባንያው ስራ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሁሉም ተሽከርካሪዎች በአካባቢያዊ ደንቦች የተደነገጉትን ሁሉንም የደህንነት መሳርያዎች ሊኖሯቸው ይገባል፣ ነገር ግን ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

- የሚሰማ ጥሩንባ።
- የመታጠፍያ ምልክቶች መብራቶች።
- የአደጋ ማስጠንቀቂያ መብራቶች።
- በቂ የመስተዋት መጥረጊያ ፈሳሽና እና መጥረጊያዎች።
- የኋላ እይታ የሚያሳዩ መስተዋቶች (የውስጥ፣ የአሽከርካሪ ጎን እና የተሳፋሪ የጎን መስተዋቶች)።
- የጭንቅላት መደገፍያ (ሊስተካከል የሚችል ወይም ቋሚ) ለሁሉም መቀመጫዎች።
- በጥሩ ሁኔታ ያሉ በአምራች የተመከሩ ጎማዎች።
- መለዋወጫ ጎማ፣ ጎማ መፍቻዎች እና ለተሽከርካሪው ክብደት የሚመጥን የመኪና ጎማ ማንሻ ክሪክ (በአገልግሎት ውል ውስጥ ካልተካተተ)
- የፊት ለፊት መስኮት እና ሁሉንም መስኮቶች ከጭጋግ ነፃ ለማድረግ የሚያስችል ቬንትሌሽን።
- የፊት ለፊት ለሚያጋጥም መጋጨት የሚቀንስ እና የተሳፋሪ ኤርባጎች (የፊት መቀመጫዎች)።
- ከደኅንነት ቀበቶ ለሁሉም መቀመጫዎች (ሦስት ነጥቦች)
- የቀን የመኪና መብራቶች (ከሌሉ የፊት መብራቶች በአሽከርካሪው መብራት አለባቸው)

የሚመከሩ የተሽከርካሪ እና የአሽከርካሪ የደህንነት መሳርያዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- በተሽከርካሪ ውስጥ የክትትል ስርዓት፣ እንዲሁም ቴሌማቲክስ ተብሎም ይጠራል መኖር አለበት። ለኤሪክሰን ተሽከርካሪዎች ፍሊት ማስተር የሚባለውን መሳርያ እንደ ተመራጭ መፍትሄ እንዲጠቀሙ ኤሪክሰን በጥብቅ ይመክራል። IVMS/የቴሌማቲክስ መሳሪያዎች የሚከተለውን መሆን አለባቸው፡-
    - አካባቢ፣ ፍጥነት፣ ፍሬን በኃይል መያዝ፣ በኃይለኛው ፍጥነት መጨመር እና ግጭቶችን ጨምሮ የተሽከርካሪውን እና የአሽከርካሪውን ባህሪ ይቆጣጠራሉ።
    - እንዳይሰይሩ ወይም ከተሽከርካሪው እንዳይወልቁ ተደርገው መገጠም አለባቸው።
    - እየከናወነ ላለው ጉዞ በቀጥታ ለመቆጣጠርና ለመከታተል የሚችል።
    - የእያንዳንዱ አሽከርካሪዎች ሪፖርቶችን ማመንጨት የሚችል።
    - በተለያዩ ወቅቶች (ቀን፣ ሳምንት፣ ወር) የተጓዙትን ርቀት እና የአየር ብክለት መጠንን የሚለካ የተሽከርካሪዎች ቁጥጥር ሪፖርቶችን ማመንጨት የሚችል።
    - የማሽከርከር ሪከርዶችን ቢያንስ ለ90 ቀናት የሚያቆዩ።
- የታሸገ የደህንነት መስታወት።
- የደህንነት ቀበቶ ማስጠንቀቂያ አላርም (የደህንነት ቀበቶ ለማያስሩ ተሳፋሪዎች)።
- የጎን ወይም እንደ መጋረጃ የሚያገለግሉ ኤርባጎች።
- ወደ ኋላ ሲያሽከረክሩ የማስጠንቀቂያ ዘዴ (ለአሽከርካሪዎች ከመኪና ኋላ ስላሉ ነገሮች የሚያስጠነቅቅ)።

 © Ericsson AB 2025 

- የኋላ ካሜራ (ወደ ኋላ ሲያሽከረክሩ የሚታይ)።
- የዝቅተኛ የጎማ ግፊት ማስጠንቀቂያ።
- መኪኖች ጎማቸው እንዳይቆለፍ የሚረዳ ሲስተም (ABS)።
- መኪና እንዳይንሸራተት የሚያረጋጋ ሲስትም (ESC)።
- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የሚመጡ ጥሪዎች እና መልእክቶች የሚያግድ ዘዴዎች/አፕሊኬሽኖች (ለሞባይል ስልኮች)።
- አሽከርካሪዎች ትኩረት እንዲያደርጉ የሚያስጠነቅቁ ወይም የሚከታተሉ ሲስተሞች።

መኪኖች የሚከተሉትን ነገሮች ማሟላት አለባቸው፡-

- የድንገተኛ አደጋ ቁሳቁስ (ማለትም ኮኖች ወይም የማስጠንቀቂያ ትሪያንግል፣ የእጅ ባትሪ፣ ወዘተ)
- በአካባቢያዊ ደንቦች የሚያዘውን ቁሳቁሶች ያሉት የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ቁሳቁስ።
- የአካባቢ ደንቦችን ያሟላ የእሳት ማጥፊያ፣ ግን ቢያንስ አንድ ኪሎግራም (ሁለት ፓውንድ)፣ ኤቢሲ ደረቅ ኬሚካል፣ እና በትክክል የተስተካከለ መሆን አለበት።

የእይታ ማሳያ ስክሪኖች ለሬድዮ ሽፋን ዳሰሳዎች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ እነዚህ ስክሪኖች በተሽከርካሪዎች ፊት ለፊት አሽከርካሪውን በማያዘናጉበት መቀመጥ አለባቸው።

## 4.2 ከዋና መንገድ ውጭ ላሉ መንገዶች የተሰሩ ተሽከርካሪዎች ያሏቸው የደህንነት መሳርያዎች፡-

ከላይ ከተጠቀሱት መስፈርቶች በተጨማሪ ከዋና መንገድ ውጭ ላሉ መንገዶች የተሰሩ ተሽከርካሪዎች የሚከተሉትን ያሟሉ መሆን አለባቸው፡-

- የጎንዮሽ ግጭት ማርገብያ ዘዴ።
- ከምሰሶ ጋር የመጋጨት ተጽዕኖ ማርገብያ መስፈርቶች።
- ተሽከርካሪው ወደኋላ እየሄደ እንደሆነ የሚያስጠነቅቅ የማስጠንቀቅያ ድምጽ።
- መኪናው ከሩቅ እንዲታይ የሚያስችሉ አንጸባራቂ ነገሮች።
- ለተሳቢዎች፡- አንጸባራቂ ነገሮች፣ ከተሳቢው ኋላ ከስር የሚበየድ ብረት ወይም ፈረፋንጎ፣ ከሚጎትተው ተሽከርካሪ ጋር የሚስማማ መንጠቆ መሳሪያ።
- የውስጥ እና የውጭ ቀርቃሪ።
- ለሁሉም አይነት መንገዶች የሚሆኑ ጎማዎች።
- በቀን የሚበሩ መብራቶች።

## 4.3 መጎተት፣ ተሳቢዎች እና ከመጠን በላይ የሆኑ ጭነቶች።

- ሌሎች ተሽከርካሪዎችን መጎተት ሁልጊዜም በየመጎተት ሙያዊ አገልግሎት በሚሰጥ ሰው/ተሽከርካሪ በኩል መከናወን አለበት።

- ተሳቢ ለመጎተት አስፈላጊ ከሆነ ዝቅተኛ መስፈርቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡-

- የሚጎተተው ተሽከርካሪ ለዓላማው የሚመጥን እና ለተሳቢው ወይም ለሚጎተተው መሳሪያ መጠን ተስማሚ መሆን አለበት።
- የተሳቢው አጠቃላይ ክብደት ከሚጎተተው ተሽከርካሪው ክብደት መብለጥ የለበትም።
- ከፍተኛው አቅም በተጎታች አካል ላይ በግልጽ መጻፍ አለበት።

- የሚጎተቱ ተሳቢዎች እና ጭነቶች ከተሽከርካሪ የመጎተቻ መሳርያ አቅም በላይ መሆን የለባቸውም።
- የመጎተቻ ዘዴው (መሳርያ) መገጠም ያለበት በተሽከርካሪው አምራች መስፈርት እና ደረጃ አሰጣጥ መሰረት ብቻ ነው። ሌላ አይነት የብረት ዘንጎች እና ሰንሰለቶችን መጠቀም የተከለከለ ነው።
- ሁሉም የሚጎተቱ ተሳቢዎች ተገቢ የሆነ የደህንነት ሰንሰለት ወይም ገመድ ሊኖራቸው እንዲሁም በሚጎተቱበት ጊዜ በደንብ መያያዝ አለባቸው፣ ይህም ዋነኛው የመጎተቻ መሳርያው ካልሰራ የመጎተት ማያያዣው/ሜካኒዝም ካልሰራ ያግዛል።
- ተሳቢው ከመጠቀምዎ በፊት የተሳቢው ፍሬን እና መብራት በትክክል እየሰራ መሆኑን ማረጋገጥ አለብዎት።
- ተሳቢዎቹ ዓመታዊ የጥገና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል።
- ማንም ሰው በተሳቢ ውስጥ ወይም በሚጎተቱ መሳሪያዎች ላይ ሆኖ እንዲጓዝ አይፈቀድለትም።
- ከመጠን በላይ የሆኑ ጭነቶች (ከተሽከርካሪው ጎን ወጣ ብለው የተጫኑ) ከአካባቢው ህግ መስፈርቶች ጋር መጣጣም አለባቸው። ምንም ልዩ መስፈርቶች ካልተገለፁ የሚከተሉትን መመሪያዎች ይጠቀሙ:-
    - ከተሽከርካሪው ጎን ወጣ ብለው በተጫኑ ጭነቶች ውጫዊው ጫፍ ላይ ሁል ጊዜ ደማቅ ቀለም ያለው ጨርቅ ይሰሩ።
    - ከመጠን በላይ የሆኑ ጭነቶች ጉዞዎን ከመጀመርዎ በፊት ምልክት የተደረገበት ሰሌዳ ሊገጠምላቸው ይገባል፣ እንዲሁም ለተገቢው የትራፊክ ባለስልጣን ማሳወቅ አለብዎት።
    - ከተሳቢው ፊት ወጣ ብለው የተጫኑ ጭነቶች ተሽከርካሪው በሚዞርበት ግዜ ከሳቢው ተሽከርካሪ ጋር እንዳይገናኙና አደጋ እንዳይፈጥሩ ተደርገው በሚገባ መጫን አለባቸው።

# 5 ሌሎች የተሽከርካሪ ዓይነቶች እና ለስራ አጠቃቀሞች።

## 5.1 ሞተርሳይክሎች (ባለ ሁለት ጎማ ተሽከርካሪዎች)።

ሞተር ሳይክሎችን ለስራ ዓላማ መጠቀም እንደ ማጓጓዣ አማራጭ ወይም እንደ ዕቃ ማጓጓዣ መጠቀም አይፈቀድም።

ሰዎች ወደ ስራ ቦታዎች ለማጓጓዝ ብቸኛው መንገድ አራቱንም ጎማዎች ማንቀሳቀስ በሚችል መኪና መሆን አለበት።

ዕቃዎች ወደ ስራ ቦታዎች መውሰድና ማጓጓዝ ያሚችሉት፣ የዕቃ መጫኛ ወለል፣ የዕቃ መጫኛ ጣሪያ ያላቸው እንዲሁም ዕቃዎችን ደህንነቱ በጠበቀ መንገድ ለማጓጓዝ የሚያስችሉ ዘዴዎች ያሏቸው አራቱንም ጎማዎች ማንቀሳቀስ የሚችሉ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተሽከርካሪዎችን ናቸው።

 © Ericsson AB 2025 

# 6 ኃላፊነቶች

## 6.1 አሽከርካሪዎች።

ሁሉም አሽከርካሪዎች የሚከተሉትን ኃላፊነቶች መረዳት እና መወጣት አለባቸው፡-

- ህጋዊ የመንጃ ፍቃድ መያዝ እንዲሁም መንጃ ፈቃዱ ከታገደ፣ ካለቀ ወይም ከተሰረዘ ለስራ ኋላፊው (PICW) ወይም ለሚመለከተው ሳይዘገዩ ማሳወቅ።
- በመንጃ ፍቃድ ምድብ መሰረት መንዳት የሚቻል ተሽከርካሪዎችን ብቻ መንዳት።
- የተመደበውን የአሽከርካሪ ስልጠና በጊዜ መቀላቀል።
- ከማሽከርከርዎ በፊት ለማሽከርከር ብቁ መሆንዎንና አለመሆንዎን ለማወቅ ሁል ጊዜ ስለራስዎ ጤንነት ራስዎን መገምገም እንዲሁም ማንኛውንም ችግር ለስራ ኋላፊው (PICW) ወይም ወደ ከሰራተኞች ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አስተዳዳሪ ማሳወቅ።
- አሽከርካሪዎች እጅግ ደክመው እያለ ወይም በአልኮል ወይም በአደገኛ ዕፆች ተጽእኖ ሥር ሆነው እያለ ማሽከርከር የለባቸውም፣ ይህም ያለ ሐኪም ማዘዣ የሚወሰዱ ወይም የታዘዙ መድኃኒቶችን ያጠቃልላል።
- በማንኛውም የስራ ቀንም ሆነ የስራ ወቅት ውስጥ ከከፍተኛው የማሽከርከር ሰዓቶች ብዛት በላይ ማሽከርከር የለብዎትም (ስለማሽከርከር የሰዓት ገደቦች ዝርዝር በክፍል 3.1 ይመልከቱ)። አስፈላጊ ከሆነ ከመናገር ወደኋላ ኣትበል፣ ለሰራተኞች ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አስተዳዳሪው ወይም ለሌላ ከፍተኛ ኋላፊነት ያለው ስራ አስኪያጅ መናገር ትችላለህ።
- አደገኛ ዕቃዎችን ወይም አደገኛ ቁሳቁሶችን ማጓጓዝ የሚቻለው በሠለጠኑ እና የተለየ ፍቃድ በተሰጣቸው እንዲሁም ከአካባቢው የቁጥጥር መስፈርቶች ጋር በሚስማማ መልኩ ብቻ ነው።
- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ትኩረት ይስጡ እና ትኩረትን የሚከፋፍሉ ተግባራት እና እንቅስቃሴዎችን ያስወግዱ።
- ራስዎን ከአደጋ በመጠበቅ ይንዱ፣ ያልተጠበቀ ነገር ሊያጋጥም እንደሚችል ይጠብቁ።
- የስጋት ጥናት እና የጉዞ ቁጥጥር እቅድ መከተል።
- የተሽከርካሪዎች ብልሽት እና አደጋዎችን በወቅቱ ሪፖርት ማድረግ።

## 6.2 የሥራ ኃላፊ (PICW) / የቡድን መሪ ወይም ተመሳሳይ ኋላፊነት ያለው።

የሥራ ኃላፊ (PICW) ማንኛውንም ተሽከርካሪ እና ሹፌር ለስራ ከማሰማራታቸው በፊት በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹትን መስፈርቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። እነዚህ የሚከተሉትን ያካትታሉ፣ በነዚህ ግን የተገደቡ ኣይደሉም፡-

- የሾፌር መንጃ ፍቃድ፣ ስልጠና እና ለስራ ብቁ መሆኑ የሚያረጋግጥ የህክምና ወረቀት ትክክለኛ መሆናቸው።
- የተሽከርካሪ ምዝገባ፣ ኢንሹራንስ እና ጥገና ወቅታዊ መሆናቸው።
- ሁሉም ተሽከርካሪዎች (ተሳቢዎች እና በቴዎችን ጨምሮ) ለስራው አላማ ተስማሚ እና ለመንገድ ብቁ መሆናቸው።

- ተሽከርካሪዎች ሁሉም የደህንነት መሳርያ ያሏቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በዚህ መመሪያ የሰፈሩ መሳርያዎች ቢያንስ ጂፒኤስ/ቴሌማቲክስን ያሏቸው መሆኑ ማረጋገጥ።
- ሁሉም አሽከርካሪዎች ስራ በሚጀምሩበት ፈረቃ ለስራ ብቁ መሆናቸው፣ ይህም የድካም ምልክት ወይም በደህንነት የመንዳት ችሎታቸውን የሚጎዳ ማንኛውንም ሁኔታ የሌላቸው መሆኑን ማረጋገጥ። ለመንዳት ብቁ ያልሆነ ማንኛውም አሽከርካሪ ከስራ መቅረት አለበት።
- የሾፌሩ የማሽከርከር ባህሪ ቁጥጥር ይደረግበታል፣ ደካማ ባህሪ ከታየም ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አስተዳዳሪው ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ።
- የስጋት ጥናት እና የጉዞ ቁጥጥር እቅድ ተካሂዶ ለአሽከርካሪዎች እና ለሚመለከታቸው ሰዎች ሁሉ ይነገራል።
- ሁሉም ክስተቶች በኤሪክሰን መስፈርቶች መሰረት በጊዜ ሪፖርት ይደረጋሉ።

## 6.3 የአቅራቢ ፕሮጀክት ኋላፊዎች።

ኋላፊዎች በኋላፊነታቸው ወሰን ውስጥ በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹት መስፈርቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። እነዚህ የሚከተሉትን ያካትታሉ፣ በነዚህ ግን የተገደቡ ኣይደሉም፦

- በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹት አስፈላጊ መስፈርቶች ለሁሉም ሰራተኞች እና አቅራቢዎች በግልፅ መነገራቸው ማረጋገጥ።
- ሁሉም ሾፌሮች በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹትን ሁሉንም አስፈላጊ መስፈርቶች ሟሟላታቸው ማረጋገጥ።
- መጥፎ የማሽከርከር ባህሪ ወዲያውኑ መፍትሄ ማግኘቱ ማረጋገጥ።
- የድካም ስጋቶች በጥሩ ሁኔታ የተያዙ መሆናቸው፣ እንዲሁም በስራዎች እቅድ ላይ ግምት ውስጥ የገቡ መሆናቸው ማረጋገጥ።
- አሽከርካሪዎች የስጋት ጥናት እና የጉዞ ቁጥጥር እቅድ መሳተፋቸው፣ አስፈላጊ እና የሚቻል ከሆነም በአካል በመገኘት መሳተፋቸው ማረጋገጥ።
- ሁሉም ከማሽከርከር ጋር የተገናኙ ክስተቶች ሪፖርት መደረጋቸው፣ መመርመራቸው፣ መንስኤዎቹ ተለይተው መታወቃቸው እንዲሁም ዳግም እንዳይከሰቱ የማስተካከያ እርምጃዎች መተግበራቸው ማረጋገጥ።
- በመመሪያው ውስጥ ያሉትን መስፈርቶች መከበራቸውን ቁጥጥር እንደተደረገበት እንዲሁም የማሻሻያ ፕሮግራሞች እንደታቀዱ እና ተግባራዊ እንደሆኑ ማረጋገጥ።

## 6.4 የተሽከርካሪዎች አስተዳዳሪ፣ የተሽከርካሪዎች አስተባባሪ፣ ወይም ተመሳሳይ ኋላፊነት ያለው

- ማንኛውንም ተሽከርካሪ እና ሹፌር ለስራ ከማሰማራታቸው በፊት በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹትን መስፈርቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። እነዚህ የሚከተሉትን ያካትታሉ፣ በነዚህ ግን የተገደቡ ኣይደሉም፦
    - የሾፌር መንጃ ፍቃድ፣ ስልጠና እና ለስራ ብቁ መሆኑ የሚያረጋግጥ የህክምና ወረቀት ትክክለኛ መሆናቸው።
    - የተሽከርካሪ ምዝገባ፣ ኢንሹራንስ እና ጥገና ወቅታዊ መሆናቸው።

- ሁሉም ተሽከርካሪዎች (ተሳቢዎች እና ቦቴዎችን ጨምሮ) ለስራው አላማ ተስማሚ እና ለመንገድ ብቁ መሆናቸው።
- ተሽከርካሪዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ የሰፈሩ ሁሉም የደህንነት መሳርያ ያሏቸው መሆኑ።
- ሁሉም አሽከርካሪዎች ስራ በሚጀምሩበት ፈረቃ ለስራ ብቁ መሆናቸው፣ ይህም የድካም ምልክት ወይም በደህንነት የመንዳት ችሎታቸውን የሚጎዳ ማንኛውንም ሁኔታ የሌላቸው መሆኑን ማረጋገጥ። ለመንዳት ብቁ ያልሆነ ማንኛውም አሽከርካሪ ከስራ መቅረት አለበት።
- የሾፌሩ የማሽከርከር ባህሪ ቁጥጥር ይደረግበታል፣ ደካማ ባህሪ ከታየም ከሰራተኞች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አስተዳዳሪው ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ።
- ሁሉም ክስተቶች በኤሪክሰን መስፈርቶች መሰረት በጊዜ ሪፖርት መደረጉ ማረጋገጥ።

# 7 ማጣቀሻዎች።

[1] መደበኛ፣ 1/155 01-LZT 138 2381፣ የሥራ ማቆም ባለስልጣን መመሪያ ለአቅራቢዎች

# 8 የተቀየረ መረጃ።

ክለሳ E። መመሪያውን በሙሉ ሙሉ ማሻሻያ ተደርጎበታል።

 © Ericsson AB 2025 